የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ከሰኔ 6 እስከ ሰኔ 13 ፣ 2017 ዓ.ም
JUNE 12– JUNE 20 /2025 G.C

## 1. ባለፉት 11 ወራት ከወጪ ንግድ ከ7 ነጥብ 21 ቢሊየን ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ

ኢ.ዜ.አ ፡ሰኔ 12/2017

በበጀት አመቱ 11 ወራት ከ7 ነጥብ 21 ቢሊየን ዶላር በላይ ገቢ ከወጪ ንግድ መገኘቱን የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።
የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) እንደተናገሩት በበጀት አመቱ በሀገሪቱ የወጪ ንግድ ታሪክ ከፍተኛ የሆነ ገቢ ተገኝቷል።
ከጠቅላላ የወጪ ንግድ 4 ነጥብ 59 ቢሊየን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ወደ ስራ መገባቱን አስታውሰው በአፈጻጸም ከእቅድ በላይ 7 ነጥብ 21 ቢሊየን ዶላር ገቢ መገኘቱን ገልጸዋል።
በበጀት አመቱ መጨረሻ ከ 8 ቢሊየን ዶላር በላይ ገቢ ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅም ጠቁመዋል።
በበጀት አመቱ 11 ወራት ከወጪ ንግድ የተገኘው ገቢ ከ2016 በጀት አመት ጋር ሲነጻጸር ከ 3 ነጥብ 96 ቢሊየን ዶላር በላይ ጭማሪ ማሳየቱንም ጠቅሰዋል።
በማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርሙ ከተሳኩ ኢኮኖሚያዊ ውጤቶች መካከል የወጪ ንግድ ዘርፍ ከፍተኛ አፈጻጸም እየተመዘገበበት መሆኑንም አክለዋል።
https://www.ena.et/web/amh/w/amh_6793193

## 2. የፍጆታ እቃዎች ድጎማን ከማህበረሰቡ ፍላጎትና አቅርቦት ጋር በማጣጣም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ዜጎች ተደራሽ ማድረግ ይገባል - ቋሚ ኮሚቴው

ሰኔ 12/2017

የፍጆታ እቃዎች ድጎማን ከማህበረሰቡ ፍላጎትና አቅርቦት ጋር በማጣጣም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ዜጎች ተደራሽ ማድረግ እንደሚገባ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ።
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 38ኛ መደበኛ ስብሰባ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የ2017 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ተወያይቷል።
የምክር ቤቱ አባላት የጥራጥሬ ምርቶች የወጪ ንግድ አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን፣ የፍጆታ እቃዎች በተለይም ከዘይትና ስኳር ስርጭት ድጎማ ጋር የተያያዙ ችግሮችን አንስተዋል።
የቅዳሜና እሁድ ገበያዎችና የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ተደራሽነት፣ እንዲሁም የጠረፍ ንግድ ስምምነቶች ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች ሊጠናከሩ እንደሚገባም ገልጸዋል።
https://www.ena.et/web/amh/w/amh_6794646

## 3. የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የሚስቡ ምቹ ሁኔታዎች

ኢፕድ፡ ሰኔ 11፣2016 ዓ.ም

ኢትዮጵያ ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ያላትን ምቹ ሁኔታ ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል። በዚህም ለካፒታል ፍሰት፣ ለቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር ወዘተ.ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ፣ በውጭ ምንዛሬ ግኝት በኩልም የራሳቸውን ዐሻራ ያኖሩ የውጭ ኢንቨስትመንቶችን ወደ ኢትዮጵያ መሳብ ተችሏል። ባለሀብቶቹም በተለያዩ ዘርፎች ተሠማርተው ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ አሁንም አዳዲስ የውጭ ባለሀብቶችን መሳብ የሚያስችሉ በርካታ ዕድሎች እንዳሏት መረጃዎች ያመለክታሉ። እነዚህን ጸጋዎች በማስተዋወቅ ወደ ኢትዮጵያ የሚሳበውን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ቁጥር ለማሳደግ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ይመክራሉ።

https://press.et/?p=153716

## 4. የኢትዮ ጅቡቲ ባቡር አ.ማ የቡና የወጪ ንግድን ለማቀላጠፍ የሚያግዙ ተጨማሪ ኮንቴነሮች አቀረበ

ኤፍ.ኤም.ሲ፡ Jun 16, 2025

መጪዎቹ ወራት የቡና እና የጥራጥሬ ምርቶችን የውጭ ንግድ ለማቀላጠፍ የሚያግዙ 104 ባለ 20 ጫማ ኮንቴነሮችን አቅርቢያለሁ አለ የኢትዮ ጅቡቲ ባቡር አክሲዮን ማህበር።

አክሲዮን ማህበሩ ከሜዲትራኒያን የባህር ትራንስፖርት ኩባንያ ጋር በመተባበር ኮንቴነሮቹን ከጅቡቲ ወደብ ወደ እንዶዴ ባቡር ጣቢያ ማጓጓዙን አስታውቋል።

የኢትዮ ጅቡቲ ባቡር አ.ማ ዋና ስራ አስፈጻሚ ታከለ ኡማ (ኢ/ር) ኮንቴነሮቹ የቡና ላኪዎች ምርቶቻቸውን በዓለም ገበያ ለማቅረብ እንደሚያስችሏቸው ገልጸው፥ በቀጣይም ተጨማሪ ኮንቴይነሮችን ለማቅረብ እንሰራለን ብለዋል።

https://www.fanamc.com/archives/294994

በውጭ ቋንቋ (English)

**5. Gov’t Bonds Set to Debut on Securities Exchange Next Month**

**The Reporter: June 14, 2025**

**ESX chief calls on diaspora to invest**

The government is preparing to roll out the sale of bonds through the newly formed Ethiopian Securities Exchange (ESX) in a move aimed at deepening domestic debt financing and attracting foreign investment.

The initiative, scheduled to begin in July 2025, marks a significant shift in short-term treasury instruments diversifications. The announcement was made by Tilahun Kassahun (PhD), CEO of the Exchange, during a high-level forum organized on June 10,2025, under the theme *Fostering Renewed Connections Between the Economy and Foreign Affairs Sectors: Towards an Enhanced Economic Diplomacy* by the Institute of Foreign Affairs.

https://www.thereporterethiopia.com/45632/

**6. Austerity over Ambition: Experts Slam Ethiopia’s New Budget as IMF-Driven Burden**

**The Reporter: June 14, 2025**

The government’s new 1.93 trillion Birr federal budget—its first since signing a USD 3.4 billion agreement with the International Monetary Fund (IMF) and World Bank last May—is drawing sharp criticism from economists and financial experts who warn it reflects foreign dictates more than local priorities.

Economic analyst KebourGhenna describes the budget as “an economic obituary for the public sector,” pointing to its lack of new infrastructure projects, domestic manufacturing stimulus, income tax relief, or meaningful support for the poor.

https://www.thereporterethiopia.com/45638/

**7. Existing Global Trade Policies Validate Urgency of Fast-tracking AfCFTA: Afreximbank**

**ENA: June 18, 2025**

President of African Export–Import Bank (Afreximbank), Professor Benedict Oramah addressed the implications of shifting global trade policies, including the reintroduction of reciprocal tariffs by the U.S., noting that such developments further validate the urgency of fast-tracking the African Continental Free Trade Area (AfCFTA).

In a powerful exchange moderated by Michael Rheinegger of the Swiss-African Business Circle on the sidelines of the Swiss-Africa Business Day, Afreximbank President joined WTO Director-General Dr. Ngozi Okonjo-Iweala for an insightful conversation on Africa’s evolving trade landscape, policy shifts, and the continent’s evolving partnerships.

Prof. Oramah emphasized that the current global trade issues highlight the critical need to expedite the AfCFTA process.

With intra-African trade still accounting for less than 18 percent of total trade, the AfCFTA provides a viable mechanism to build resilient value chains, stimulate industrial growth, and reduce reliance on external markets.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_6785445

**8. China-Africa Economic and Trade Expo: Forging a new area of partnership**

**Ethiopian Press: June 17, 2025**

The Permanent Exhibition Hall of the China-Africa Economic and Trade Expo is located in the China-Africa Economic and Trade Cooperation, Promotion, and Innovation Demonstration Park in the Yuhua Block, Changsha Area, China (Hunan) Pilot Free Trade Zone.

It is a public service platform for the exhibition and sales of African products and trade with Africa. As a major project of Hunan Province, it aims to create a perpetual China-Africa Economic and Trade Expo.

The first session of China-Africa Economic and Trade Expo (CAETE) took place in Changsha, Hunan, in June 2019. With the theme of “Win-Win Cooperation for closer China-Africa Economic and Trade Partnership”, guided by the “Eight Major Initiatives”, it focused on key areas such as trade, agriculture, investment, financing, cooperation parks and infrastructure. Over 30 activities have been conducted, including thematic seminars, professional forums, trade talks, exhibitions, and field visits, according to a source.

Representatives from 53 African countries that have diplomatic relations with China, 30 ministries/commissions under the central government, 12-plus international organizations including the African Union, and 30 provinces/municipalities/autonomous regions in China participated in the expo and exhibition

https://press.et/herald/?p=117316